2024–2025 መመሪያ

# ወደ መዋእለህፃናት ቀደምብሎ መግባት

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Maryland

## ቀደምብሎ መግባት

ቀደም ብለው ወደ መዋእለህፃናት እንዲገቡ የሚደረጉ ልጆች ከእኩዮቻቸው ይልቅ አስቀድሞ ትምህርት የመጀመር ችሎታ እዳላቸው ለማረጋገጥ የአካደሚክ ክህሎት፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ ዕድገት እንዳላቸውና ቀደም ብለው ትምህርት የመጀመር ችሎታ እንዳላቸው መታየት/ማሳየት አለባቸው። ተማሪዎች በላቀ የትምህርት ምደባ ላይ ስለሚሆኑ በትምህርቱ ጥንካሬ ተስፋ እንዳይቆርጡ በቀዳሚነት ለሚገቡ ተማሪዎች መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች ጠንካራና ከፍተኛ ናቸው። ከኦክቶበር 15 በኋላ ለተወለዱ ልጆች፣ማመልከትም ሆነ የመቀበል ሁኔታ አይኖርም።

መዋእለ ህፃናት/Kindergarten—በሴፕቴምበር 2 እና ኦክቶበር 15 መካከል 5 አመት የሚሞላቸው ልጆች ወደ መዋዕለ ህፃናት አስቀድሞ ለመግባት ብቃት ሊኖራቸው ይችላል።

የበለጠ መረጃ ለማግኘት፡- የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምርያ (MSDE) COMAR 13A.08.01.02 እና የሞንትጎመሪ ካዉንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ Policy JEB ይመልከቱ፤ ወደ ቅድመ መዋእለ ህፃናት፣ መዋእለ ህፃናት፣ እና አንደኛ ክፍል አስቀድሞ ስለመግባት  እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንብ/Regulation JEB-RB፣ ወደ ቅድመ መዋእለ ህፃናት፣ መዋእለ ህፃናት፣ እና አንደኛ ክፍል አስቀድሞ ስለመግባት።

## ወደ መዋእለ ህፃናት አስቀድሞ መግባት

### የመዋእለ ህፃናት ፕሮግራም ምን ምን ያጠቃልላል?

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መዋእለ ህፃናት ፕሮግራም የተማሪዎችን የማንበብ፣ የመጻፍ፣ እና የሒሳብ ብቃትን በሚያዳብር ሥርዓተ ትምህርት ላይ የተመሠረተ ሲሆን ለሁሉም ተማሪዎች ጠንካራ ትምህርቶችን ይሰጣል። ጠንካራ የትምህርት ፕሮግራም የሚያካትተው፡-

- በየእለቱ ማንበብ/መጻፍ/የቋንቋ ስነጥበብ ብሎክ መሥራት
- በየእለቱ የሂሳብ ብሎክ መሥራት
- በየወቅቱ የሚያሳዩትን ግስጋሴ የመከታተል ግምገማ እና ለቀጣይ ትምህርት ዝግጅት ማድረግ፣
- በአነስተኛ ቁጥር- እና ብዙ ሆነው-በቡድን ማስተማር፣ እና
- በተናጠል ለየብቻ ለመማር የሚያስችሉ እድሎች።

የትምህርት ፕሮግራሙ በተጨማሪ ሳይንስ እና ማህበራዊ ጥናት/ሶሻል ስተዲስ ያካትታል፤ እንዲሁም ተማሪዎች በስነጥበብ ሥራ፣ በሙዚቃ፣ በኢንፎርሜሽን ሊተርሲ፣ እና በጤና እና የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርቶች እንዲሳተፉ እድል ይሰጣል።

ለተጨማሪ መረጃ፣ እባክዎን ወደ አካባቢዎ ት/ቤት (ሆም ስኩል) ሄደው የመዋእለ ህፃናት የትምህርት ክፍልን ለመጎብኘት ቀጠሮ ያድርጉ።

## አስቀድሞ መዋእለ ህፃናት መግባት የተሻለ አማራጭ ነው ወይ?

### እባክዎን የሚከተሉትን ያገናዝቡ፡-

- አስቀድሞ መዋእለ ህፃናት የመግባት ሂደት አላማ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በሚከናወኑ ግምገማዎች መሰረት፣ ከአማካይ ደረጃ በላይ አፈፃፀምና እድገት የሚያሳዩ ህጻናት ልጆች ወደ መዋእለ ህፃናት እንዲገቡ ማስቻል ነው። የልጁ/የልጅቱ ትምህርት የመቀበል ችሎታ እና ማህበራዊ/ስሜታዊ እድገት ግምት ውስጥ ይገባሉ።
- እነዚህ በእድሜ አነስተኛ ልጆች በመማርያ ክፍል ውስጥ በአንድ አመት ወይም ከዚያ በላይ ከሚበልጧቸው ልጆች ጋር አብረው መስራት መቻል ይኖርባቸዋል።
- ተማሪዎች ከአቅማቸው በላይ ትምህርት እንዲማሩ በመመደባቸው ተስፋ እንዳይቆርጡ ለማረጋገጥ አስቀድሞ ለመግባት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች ከፍተኛ ናቸው።
- ት/ቤት አስቀድሞ መግባት ወላጆች/አሳዳጊዎች ለልጃቸው የሚያደርጉት የረጅም ጊዜ ውሳኔ ነው። በኤሌሜንታሪ፣ በመካከለኛ ደረጃ፣ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች እና ከዚያም ባሻገር በሚያልፉበት ወቅት በልጁ/በልጅቱ ማህበራዊና/ስሜታዊ ሁኔታዎች ላይ ምን አይነት እምቅ ተፅእኖ እንደሚያስከትል መተንበይ አይቻልም።
- አስቀድሞ መዋእለ ህፃናት ማስገባት ልጆች የሚያስፈልጋቸውን እንክብካቤ መተኪያ ማለት አይደለም። ወላጆች/አሳዳጊዎች ስለ ህጻናት እንክብካቤ መረጃ፣  "LOCATE" ማነጋገር ያስፈልጋቸዋል፡- ስለ ህጻንት እንክብካቤ 877-261-0060 ይደውሉ ወይም http://www.marylandfamilynetwork.org/programs-services/locate/ ኢ-ሜል አድርገው በአካባቢ ፈቃድ ያላቸው የህጻናት እንክብካቤ ሰጪዎችን ዝርዝር ማግኘት ይችላሉ።

## ከሌሎች መዋእለ ህፃናት ከሚገቡ ልጆች ተለይተው ቀድሞ ለመግባት ለሚያመለክቱ ህጻናት ግምገማ የሚደረገው ለምንድነው?

በሜሪላንድ ስቴት ደንብ (COMAR 13A.08.01.02) መሠረት፣ ሴፕቴምበር 1 ላይ ወይም ቀደም ብሎ 5 ዓመት የሚሞላቸው ልጆች መዋእለ ህፃናት እንዲገቡ የዕድሜ ብቃት ይኖራቸዋል። በስቴት መመሪያ መሰረት፣ የልደት ቀኑ(ኗ) በሴፕቴምበር 2 እና ኦክቶበር 15 መካከል የሆነ(ች) ልጅ አስቀድሞ እንዲገባ ወይም አስቀድማ እንድትገባ ሊፈቀድ ይችላል። የልደት ቀናቸው ከኦክቶበር 15 በኋላ ለሆኑ ልጆች ምንም አስተያየት አይደረግላቸውም። ልጅ የተወለደ(ች)በት ቀን ከኦክቶበር 15 በኋላ ከሆነ የይግባኝ ሂደት አይኖርም።

ዕድሜአቸው ብቁ ያልሆኑ ልጆች ወደ መዋእለ ህጻናት ቀደም ብለው ለመግባት ከአማካይ ደረጃ በላይ አፈጻጸም ማሳየት እና ብቁነታቸው በመዋዕለ ሕፃናት የዓመቱ መጨረሻ መመዘኛዎች ላይ መረጋገጥ አለበት። ለቀዳሚ የህጻናት እድገት ግምገማ ህጻናት/ልጆች ማጥናት ወይም የተለየ ዝግጅት ማድረግ አያስፈልጋቸውም። ግምገማዎቹ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የእድገት ዘርፎች የእያንዳንዱን ልጅ አኳኋን የሚመዝኑ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ያጠቃልላሉ፡-

- የአእምሮ እድገት
- የንባብና የቋንቋ እድገት
- የሂሳብ እውቀት አስተሳሰብ

## ከግምገማ ሂደቱ ምን ይጠበቃል?

ቅድመ መዋእለ ህጻናት አስቀድሞ ለማስገባት የሚደረጉት ግምገማዎች በሙሉ የሚከናወኑት ከማርች 18 እስከ ጁላይ 31፣2024 ባለው ጊዜ ውስጥ ነው። ግምገማው በአከባቢ ትምህርት ቤት ህንጻ ውስጥ በአካል ይደረጋል። ትምህርት ቤቶች የማረጋገጫ ምዘናዎችን የማካሄድ ቀጠሮ ለማስያዝ ከወላጆች/ከሞግዚቶች ጋር ይነጋገራሉ። እያንዳንዱን ልጅ ለመገመገም የሚቻለው አንድ ጊዜ ብቻ ነው። የማጣራት ምዘና በሚደረግበት ጊዜ ወላጆች/ሞግዚቶች ልጃቸው ጤነኛ እንደሆነ(ች) እና በምዘናው ተግባር መሳተፍ እንደሚችል-እንደምትችል የሚገልጽ ቅጽ እንዲፈርሙ ይጠየቃሉ። ልጆች በማጣርያ ሂደቱ

ከመሣተፋቸው በፊት ወላጆች/ሞግዚቶች ትምህርት ቤት አስቀድሞ ስለመግባት ሂደት ለልጃቸው በመንገር ስነልቡናዊ ዝግጅት ማድረግ ይኖርባቸዋል። በማጣርያው መሳተፍ ማለት ለመጪው የትምህርት ዓመት  ወደ መዋእለ ህጻናት በቀጥታ ያስገባዋ(ታ)ል ማለት እንዳልሆነ ለልጃቸው በግልጽ ማሳወቅ አለባቸው። የማጣርያ ምዘናዎች የሚካሄዱት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች አማካኝነት ነው። ልጆችም ሆኑ ሠራተኞች ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ለእያንዳንዱ ህጻን ለየብቻ ለማጣራት የሚጠቀሙበት ዕቃ ይኖራል።

ፊት ለፊት በአካል ማጣራት የሚደረግላቸው ልጆች በወቅቱ ወላጆች/ሞግዚቶች አብረው ላይገኙ ይችላሉ። ት/ቤቱ መቆያ ቦታ ያዘጋጃል።

ውጤቱ በማጣሪያው እለት አይሰጥም። የት/ቤቱ ቡድን የግምገማውን አሃዞችና መረጃዎች ከገመገሙ በኋላ15 ቀናት ውስጥ ውሳኔአቸውን የሚገልጽ ፅሁፍ ይደርሳል። ቀደም ብሎ ስለመግባት የሚደረገውን አስተያየት/ሪኮመንዴሽን በተመለከተ የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ ወላጅን ወይም አሳዳጊን ያነጋግራል።

## አንድ ወላጅ/አሳዳጊ ልጃቸው ወደ መዋእለህጻናት አስቀድሞ መግባት እንዲችል/እንድትችል እንዴት ማመልከት ይችላል?

- ልጃቸው ወደየትኛው MCPS የአካባቢ ት/ቤት እንደሚገባ/እንደምትገባ መጀመሪያ ወላጆች/ሞግዚቶች ማወቅና መወሰን አለባቸው። እርስዎ የሚኖሩበት አካባቢ ት/ቤት የሚያገለግለውን ክልል መረጃ ለማግኘት ከሰኞ እስከ ዓርብ 9:00 a.m. – 12:00 p.m በስልክ ቁጥር፡- 240-314-4700 ደውለው ይጠይቁ። በተጨማሪም MCPS ድረ-ገጽ ላይ የሚገኘውን የት/ቤት ምደባ ዝርዝር መፈልጊያ መጠቀም ይችላሉ፡- www.montgomeryschoolsmd.org  የቦርድ ፖሊሲ JEA፣ መኖሪያ ሠፈር፣ የትምህርት ክፍያ፣ እና ምዝገባይመልከቱ።
- ከዚያም ወላጆች/ሞግዚቶች ልጃቸውን ወደ መዋእለ ህጻናት አስቀድመው ለማስገባት (MCPS Form 271-6 መዋእለ ህጻናት አስቀድሞ ማስገቢያ ማመልከቻ/Application for Early Entrance to Kindergartenሞልተው ለልጃቸው የአካባቢ ት/ቤት ማቅረብ አለባቸው።
- ማመልከቻውን ከሚከተሉት ቦታዎች ማግኘት ይቻላል፡-
  - ከአካባቢዎ ትምህርት ቤት (ሆም ስኩል)
  - MCPS ድረ-ገጽ http://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/forms/pdf/271-6.pdf
- ወላጆች/ሞግዚቶች ተጠናቆ የተሞላ ማመልከቻ ለልጃቸው ሆምስኩል ማቅረብ አለባቸው።
- ማመልከቻዎችን ከፌብሩዋሪ 1 እስከ ጁን 30 ድረስ እንቀበላለን።

## ወላጆች/አሳዳጊዎች ስለ ት/ቤቱ ውሳኔ ተጨማሪ መረጃ እንዴት ማግኘት ይችላሉ?

- ስለ ት/ቤቱ ውሳኔ ተጨማሪ መረጃ የሚፈልጉ ወላጆች/አሳዳጊዎች ስለ ማጣርያ ውጤቶቹ ሊነጋገሩባቸው እና ማንኛውንም ተጨማሪ መረጃ ለመጋራት ከት/ቤቱ ርእሰመምህር ጋር ስብሰባ ማድረግ ከፈለጉ መጠየቅ ይችላሉ።

## ህዝባዊ ስላልሆኑ አማራጭ የህጻናት እንክብካቤ ሰጪዎች የስቴቱ መመርያዎች ምንድን ናቸው?

- MSDE ድንጋጌ መሰረት፥ ህጻናት መዋእለ ህፃናት ለመግባት በእድሜ ብቁ ለመሆን ከሴፕቴምበር 1 በፊት 5 አመት ወይም ከዚያ በላይ መሆን አለባቸው። በተጨማሪም በእድሜ ብቃት ህፃናት ወደ ህጻናት ማሳደጊያ/ነርሰሪ ት/ቤት ለመግባት ሴፕቴምበር 1 ላይ 3  አመት ወይም ወደ ነርሰሪ ት/ቤት ፕሮግራም ለመግባት 4 አመት እንዲሆናቸው ደንቡ ይደነግጋል።

## ተጨማሪ የመዋእለ ህፃናት ፕሮግራም መረጃ የት ይገኛል?

ስለ መዋእለ ህጻናት ስርዓተ ትምህርት ዝርዝር መረጃ እና ከፕሮግራሙ ስለሚጠበቁ ጉዳዮች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች በዚህ MCPS ድረገጽ የመዋእለ ህጻናት መረጃ እና ሪሶርስ ገጽ ላይ መመልከት ትችላላችሁ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/enroll/kindergarten/

ስለ መዋእለ ህጻናት የሜሪላንድ ስቴት ስርአተ ትምህርት/ከሪኩለም ዝርዝር ለማወቅ ይህንን MSDE ድረገጽ ይጎብኙ፡- www.marylandpublicschools.org

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር፣ በብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሃረግ፣ በብሔር፣ በብሔራዊ ማንነት፣ በዜግነት፥ በኃይማኖት፥ በስደተኝነት ሁኔታ፣ በፆታ፣ በጾታ መገለጫ፣ የፆታዊ  ስሜት መገለጫ፣ የቤተሰብ መዋቅር፣ በወላጅ ሁኔታ፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በችሎታ፣ በእድሜ፣ በማኅበራዊ  ስሜታዊነት እና በአካላዊ ሁኔታ፣ በድህነት እና በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፣ እንዲሁም በቋንቋ ላይ የተመሠረተ ወይም ሌሎች በሕግ ወይም በህገመንግስት የተጠበቁ/የተከበሩ ባህሪያትን ወይም ትውፊቶችን ጨምሮ ማናቸውንም አይነት ሕገ ወጥ መድሎን ይከለክላል። ስለ አድሎአዊነት ጥያቄዎች ካሉ/መረጃ ለመፈለግ ወይም ቅሬታዎችን ለማቅረብ፣ ወይም አመቺ/ተስማሚ ስፍራ ለመጠየቅ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የጸረ-መድሎአዊነት መግለጫ ከመመሪያዎች እና የኮሙኒኬሽን መረጃዎች ጋር በዚህ ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል፡- http://www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination/

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

Department of PreK–12 Curriculum and Districtwide Programs ከመዋእለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል የሥርአተ ትምህርት እና ዲስትሪክት አቀፍ ፕሮግራሞች
Office of Curriculum and instructional Programs የስርአተ ትምህርት እና የማስተማር ፕሮግራሞች ቢሮ
0561.24ct • Editorial, Graphics & Publishing Services • 1/24 • 255